# ሰሞነኛ (ልዩ ዕትም)
## የግንቦት   መልዕክት

ከዛሬ 16 ዓመታት በፊት የዴሞክራሲአዊ መንገዱ የተዘጋባቸው ታጋይ ሃይሎች በመሣሪያና በወታደር ሃይል በሀጉረ-አፍሪካ ግዙፍ የሚባለውን የፋሽታዊ ደረግ ሃይል በተጠናከረ ህዝባዊ ድጋፍ ገርስሰው ለመጣል ችለዋል፡፡ይሄው ህዝባዊ ድል በህዝብ ዙሪያ መለስ ተሳትፎ መድመቁ የሚያመለክተው በወቅቱ የነበረው አገዛዝ በህዝብ ሰባዓዊና ዴሞክራሲአዊ መብቶች ላይ ሲያደርግ የነበረው ግፍና ሰቆቃ ስርዓቱ መግዛት የማችልበት ደረጃ መድረሱን ነበር፡፡

ኢህአዴግ የደርግን ወታደራዊ አገዛዝ ከጣለ በኋላ በወቅቱ ለሰሚና ለተመልካች አሰፈሪ የነበረውን የተበተነ የጦር መሳሪያ መልክ ማስያዝ ነበረበት፡፡ይህ ተግባር የህዝቡን ሙሉ ተሳትፎ የተላበሰ ነበርና አንዳንድ የጠረጴዛ ፖለቲከኞችና ተንታኞች እንደተነበዩልን አገራችን እንደ ሱማሌና አፍጋንስታን ሳትሆን ቀረች፡፡

ቀጥሎም የአትዮጵያ ህዝቦችን ስብዓዊና ዴሞክራሲዊ መብት እንዲሁም የህዝቦቿን እኩልነት የሚያስከብር ህገ መንግስት ተረቅቆ በህዝብ ተሳትፎ እንዲፀድቅ ተደረገ፡፡አገሪቱ ዘወትር በማያባራ ጦርነት ሊዳርጋት የሚችለውን የህዝቦችን ነፃነትንና እኩልነትን የመቀበልና የማረጋገጥ ጥያቄ ያለምንም ማወላወልና ገደብ ተግባራዊ መሆን ችሏል፡፡በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችን  መሰረት ያደረገ የክልል መንግስታት  በማቋቋም  የራስን  በራስ የማስተዳደር መብት በአገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ተረጋግጧል፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት የአገራችን ዋነኛ ጠላት ድህነትና ኋላቀርነት መሆኑን በመገንዘብ ሰፋፊ የልማት መርሃ ግብሮችን በመንደፍ ምርትና ምርታመነትን ለማሳድግ በሰፊው ተንቀሳቀሷል፡፡በዚህም መሰረት የአገሪቱ የኢኮኖሚ ጀርባ የሆነው የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ትርጉም ያለው ለውጥ እንዲያሳይ ፣ በጥቂት የልማት ጣቢያ ባለሞያዎች የተጀመረው እንቅስቃሴ ዛሬ በእየአንዳንዱ የገጠር ቀበሌ የልማት ጠቢያ ሰራተኞችን በመመደብ ለአርሶ አደሩ የቅርብ ሞያዊ ድጋፍ በመስጠት ምርትና ምርታማነት እንዲያድግ መሰረቱን ለመጣል ተችሏል፡፡



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd # 308  Los Angeles, CA 90010
Tel: 213 365 6651  Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org

ከዚሁም ጋር ለኃላቀርነታችን ምክንያት የሆኑትን እንዲሁም በቀዳሚ ትኩረት አድርገን የያዝነውን የግብርናና በግብርና ላይ የተመሰረተ የኢንዲስትሪ ልማትን ሊያፋጥኑልን የሚችሉትን ተስማሚ የትምህርት፣የጤና እንዲሁም የመሰረተ ልማት ፖሊሲዎች በመደፍና ሰፊ የሆነ ሀብትና የሰው ጉልበት በማንቀሳቃስ ከዕድገታችን ጋር ለማዋደድ የሚያስችል ስራ ተከናውኗል::

ባለፉት 16 ዓመታት በሁሉም ዘርፎች አገራችን በተሻለ የዕድገት ደረጃ እየተጓዘች መሆኑን በተጨባጭ የሚያሳዩ እንቅስቃሴዎች መደረጋቸውን የአገር ውስጥና የውጭ የኢኮኖሚ እድገት ጠበብቶች ሳይቀሩ መስክረዋል::

እነዚህ የተለያዩ የልማት ተግባራት ሲከናወኑ ግን ያለአናዳች እንከን አልነበረም:: ከሁሉም በላይ አዳዲስ ነገር ሲጀመሩ ፈጥኖ ለመቀበል ያለመቻልና የተጠራጣሪነት ባህሪያት በፈጣን ሁኔታ የጀመረውን የልማት ጉዞ የሚፈታተኑ ጉዳዮች ነበሩ::በአርሶ አደሩ ማሳ ላይ ማዳበሪያ፣ ዘመናዊ አስተራረስ ዘዴና ምርጥ ዘር መጠቀሙ ይሄው እንደዛሬው በሰፊው ከመለመዱ በፊት ብርቱ ፈተናዎችን ማለፍ ጠይቋል::ማሳ ያደርቃል፣ማዳበሪያ የነካ መሬት ተመልሶ ለማረስ አይቻልም ከሚለው ጀምሮ ምርቱ ከተመረተ በኃላ በላተኛ የለውም እስከሚለው ቅስቃሳ ድረስ የነበረውን የግንዛቤ ችግር ለማስተካከል ሰፊ የሆነ አርሶ አደሩን ማዕከል ያደረገ ሁለ ገብ ሥራ ተሰርቷል::

ከዚሁም ጋር በየጊዜው የሚደቀነውን የመልካም አስተዳደር ችግር በሰላና ተከታታይነት ባለው የሥራ ግምገም ለማስወገድ ቢሞከርም ፣ከድህነታችንና ከአጉል ልማዶቻችን ስፋት አንፃር ችግሮቹ አሁንም ድረስ የሚታዩና ያልተፈቱ ናቸው::መልካም አስተዳደርንና አገልግሎት አሰጣጥን በመንግስት መ/ቤቶች በተሳለጠ መልክ ለማስፋፋት የሲቨል ሰርቪሱ ሪፎርም ፕሮግራም ተንድፎ ተጨባጭ ለውጦች መታየት ቢጀምሩም ፣ ሁሉም ፈፃሚ አካል በዕምነት ይዞ የማይነወጥ የአሰራር ስርዓት በመፍጠር ግን በተከታታይ መስራት ያለብን ጉዳይ መሆኑ ዕሙን ነው::

አገራችን የብዙ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች አገር በመሆኗ ፣ ይህንኑ ህዝባዊ መስተጋብርና አኗኗር መሠረት ያደረጉ የክልል አስተዳደሮች ተዋቅረው ህዝቡ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳደር ብቻ ሳይሆን ለዘመናት ተማክሎ የኖረው የስልጣን ምንጭና ሃላፊነት በግልፅ በተቀመጠ ህገመንግስታዊ መርህ በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የህዝቦች እኩልነትና ነፃነት እንዲከበሩ አድርጓል::ይህም በአገራችን በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተውን አንድነት ያጠበቀው መሆኑን ማየት ይቻላል::ይሁን እንጂ በተዋቀሩ



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org

አስተዳደሮች የበቃ የሰው ሃይል፣የጠራ አመለካከትና የተስተካከለ የሃብት አጠቃቀም ችግሮች ጨርሰው የሉም አይባልም።

የዘንድሮውም ግንቦት ሃያ አገራችን አዲሱን ሚሊኒየም በዓል ለማክበር ዝግጂት በምታደርግበት ጊዜ የሚከበርና የሚታወስ በመሆኑ ለሚኒየም በዓል የገባናቸውን ቃል-ኪዳኖች ሁሉ ለዚሁ ቀንም መታሳቢያ ይሆናሉ።

ከዚሁም ጋር በአሁኑ ጊዜና ስዓት የአገራቸውን ችግር ለመቅረፍ ደፋ ቀና የሚሉትን፣ በተለያያ የልማት ተግባራት በመሰማራት ተጨባጭ ለወጥ ለማምጣት የሚጥሩትን፣ የጀመሩት ትልም አገርን ከድህነት የሚያላቅቅ በመሆኑ በጊዜአዊ ችግሮች ሳይደናቀፉ እንዲቀጥሉ አደራ እንላለን።

የአገርን አንድነት ለመሸርሸር ከሚያሴሩ ጠላቶቻችን ጋር በመተናነቅ ሰላማችን በአስተማማኝ ደረጃ እንዲገኝና ጠላቶቻችን ደግሞ የጀመሩት እኩይ ዓላማ እራሳችውን የሚያጠፋቸው መሆኑን በአገራዊው ተጋድሎው ያስመሰከረው ጀግናው የመከላከያ ሰራዊታችን ፣ አሁንም በሚያስመዘግበው ድል የኮራን መሆናችን ስንገልፅለት ፣በማንኛ ውም አገራዊ ግዳጅ ምን ጊዜም ከጎኑ የቆምን መሆናችን ስንገልፅ አሁንም በድጋሜ በኩራት ነው።

በአጠቃላይ የአገራችን ሰላምና የህዝባችን ደህንነት ለማተራመስ በሚሯሯጡ አለም አቀፍ ሽብርተኞች ላይ ድል በተጎናፀፍንበት ማግስት በምናክበረው ግንቦት ሃያ ለዴሞክራሲአዊና ህዝባዊ ዓላማ ሲሉ መስዋዕት የሆኑ ወገኖቻችን የሰጡንን አደራ ተግባራዊ እንድናደርግ ይቀሰቅሰናል።የለማችና ከድህነት የተላቀቀች ኢትዮጵያን እንድንገነባ አደራ ይለናል። በህዝቦቿ እኩልነትና መፈቃቀድ አድነቷ የታነፀ ፣ እንዲሁም በአለም ሰላም ወዳድ ህዝቦች የተከበረች አገር እንድንመሰርት ያተጋናል።ከአረፉበት የጀግንነት መስዋዕት ቦታ ቀና ብለው በነፋስ ሃይል የሚወዛወዘውን ማሳ ይጠቁሙናል።

እናም ፣ የጀግኖች ሰማዕታት አደራ በላ እንዳንሆን የአገራችን አበሳና መከራ ለመቅበር እንነሳ። ወቅቱም ፣የግንቦት ጥሪም ይሄው ነውና!!



Bi-monthly news bulletin prepared by the Consulate General of Ethiopia
3460 Wilshire Blvd # 308 Los Angeles, CA 90010
Tel: 213 365 6651 Fax:213 365 6670 info@ethioconsulate-la.org
www.ethioconsulate-la.org